# ስለ ልዩ ኣማራጭ እድል ጠቃሚ መረጃ

**ልዩ ኣማራጭ ዕድል ምንድነው**

ለVCE ወይም VCAL ተማሪዎች በህመም፣ በኣካል መጉደል ወይም በሌላ ችግር ምክንያት ለሚጎዱ ተማሪዎች የልዩ ኣማራጭ እድል ያገኛሉ። ልዩ ኣማራጭ እድሉን እንዲያገኙ የሚፈቀድላቸው ተማሪዎች በፕሮግራሙ የመሳተፍና የተማሩትን በተግባር የሚያሳዩበት እድል ይፈጥርላቸዋል።

**የልዩ ኣማራጭ እድል የሚተገበርባቸው የሚከተሉት ናቸው፤**

- በክፍል ውስጥ በሚካሄድ ትምህርት ላይ
- ትምህርት ቤት መሰረት ያደረገ ምዘና ሲደረግ
- የVCE  የውጭ ምዘና ላይ ሲከናወን

ተማሪዎች ይህንን ኣማራጭ እድል የሚያገኙት ቀጥሎ ለተመለከቱት ችግሮች የተጋለጡ ሲሆኑ ነው።

- ኣጣዳፊ ወይም የቆየ ህመም ላለባቸው
- የግል ወይም የቤተሰብ ችግር ላለባቸው
- ሌሎች እክሎች ወይም የኣካል መጉደል፣ የመማር ችሎታ መዛባት ያለባቸውን ጨምሮ የዚህ ኣማራጭ ዕድል ተጠቃሚዎች ናቸው።.

የትምህርት ውጤታቸው በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ለምሳሌ ለረጅም ጊዜ ከት/ቤት በመቅረታቸው ምክንያት ውጤታቸው በጣም ያሽቆለቆለባቸው ተማሪዎችም በዚህ ኣማራጭ እድል እንዲያገኙ ይደረጋል።

**ይህን ልዩ ኣማራጭ እድል ሲሰጥዎ ምንድነው የሚሆነው?**
ልዩ ኣማራጭ ዕድሉ ቀጥሎ የተመለከቱት ገፅታዎች ሊኖሩት ይችላል።

- የክፍል ስራ መጨረስና ትምህርታዊ ምዘናውን  በተለየ ጊዜ እንዲሆን ማድረግ
- ስራውን ለመጨረስም ሆነ ለምዘናው ተጨማሪ ጊዜ መስጠት
- የተለየ የትምህርታዊ ምዘና መንገድ መጠቀም ወይም የተለየ ስራ መስራት
- ለክፍል ትምህርቱም ሆነ ለትምህርታዊ ምዘናው የሚረዳ ተጨማሪ ቴክኖሎጂ ፣ ኢጋዥ ወይም የተለየ ዝግጅት መጠቀም።
- ተማሪው በሌላ ስራ ያገኘውን ውጤት ኣመዛዝኖ የተመጣጠነ ውጤት መስጠት።

**የልዩ ኣማራጭ እድሉን ለማግኘት  እንዴት  ያመለክታሉ?**
ይህ ልዩ ኣማራጭ እድል ይገባኛል የሚል እምነት ካልዎት፤የትምህርት ቤትዎ ርዕሰ መምህርን ወይም የVCE ኣስተባባሪን ያነጋግሩ። ትምህርት ቤትዎ ይህ የልዩ ኣማራጭ እድል በክፍል ውስጥ ለሚማሩትም ሆነ  ወይም ለመደበኛው የትምህርት ቤት ምዘና የሚገባዎ መሆን ኣለመሆኑ ይወስናል።

የቪክቶሪያ ስርዓተ ትምህርትና የምዘና ባለስልጣን / Victorian Curriculum and Assessment Authority (VCAA) እርስዎ ለVCE ለውጭ ምዘና ፤ ኣጠቃላይ የውጤት ፈተናን (GAT) ጨምሮ የልዩ የፈተና ዝግጅት  የሚመለከትዎ መሆን ኣለመሆኑን የመወሰን ስልጣን ኣለው። ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ወክለው ለልዩ ፈተና ዝግጅት ማመልከቻ የማቅረብ ሃላፊነት ኣለባቸው።

ስለ ልዩ ኣማራጭ ዕድል በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ በVCAA ድረገፅ https://www.vcaa.vic.edu.au/ ማግኘት ይችላሉ።
በተጨማሪም VCAA ን

- በስልክ ቁጥር : 9032 1629 ይደውሉ (የብሄራዊው የስልክ ኣስተርጓሚዎች  የስልክ ቁጥር በ131 450).ይደውሉ እንዲሁም
- በኢሜይል ፡ vcaa@education.vic.gov.au መላክ ይችላሉ።

የቪክቶሪያ ስርዓተ ትምህርትና የምዘና ባለስልጣን / Victorian Curriculum and Assessment Authority (VCAA) የሚከተሉትን ተግባራት የሚያከናውን የመንግስት ኣካል ነው።:

- በቪክቶሪያ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን ኮርስ ያዘጋጃል።
- የቪክቶሪያ የትምህርት የምስክር ወረቀት (VCE) እና የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት የምስክር ወረቀት (VCAL)ያቅዳል ምዘናውንም ይመራል።